የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 28
ADDIS ABABA 29th June, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፯/፪ሺ፲፫ ዓ.ም

የፌዴራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት እና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ አዋጅ..........ገጽ ፲፫ሺ፪፻፷፰

## Content

Proclamation No. 1247/2021

Federal Government Supplementary Budget and Financing Restructuring Proclamation....page 13268

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፯/፪ሺ፲፫

## የፌዴራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት እና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭(፩)፣(፲፩) እና በኢትጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀፅ ፳፯ መሰረት ለተጨማሪ መደበኛና ካፒታል ሥራዎች እንዲሁም ለ፪ሺ፲፫ በጀት ዓመት ከበጀት ድጋፍ የሚገኘው ገቢ በመቀነሱ ከሀገር ውስጥ ቀጥታ ብድር በመሸፈን የወጪ አሸፋፈንን ለማስተካከል የሚከተለው ታውጇል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩</u>** ይህ አዋጅ የ፪ሺ፲፫ በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፯/፪ሺ፲፫ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 1247/ 2021

## FEDERAL GOVERNMENT SUPPLEMENTARY BUDGET AND FINANCING RESTRUCTURING PROCLAMATION

In accordance with Article (55) (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and in accordance with Article 27 of the Federal Government of Ethiopia Financial Adminisration Proclamation No 648/2009 a supplementary of Recurrent and Capital Budget and financing restructuring due to the reduction of external budget support for deficit financing from domestic borrowing approved for the 2013 E.C budget year is hereby proclaimed.

**Article 1** This Proclamation may be cited as the 2013 Fiscal Year Supplementary Budget Proclamation No. 1247/2021.

**አንቀጽ ፪** ከሐምሌ ፩/፪ሺ፲፪ ጀምሮ ሰኔ ፴/፪ሺ፲፫ በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በፌዴራል መንግሥት ከሚገኘው ገቢ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፦

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ ለመደበኛ ወጪዎች | ብር | 25,833, 000,000 |
| ለ/ ለካፒታል ወጪዎች | ብር | 602,375,000 |
| ሐ/ የወጪ አሸፋፈን ለማስተካከል | ብር | 12,044,900,000 |
| ድምር | ብር | 38,480,275,000 |

ሠላሳ ሥምንት ቢሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር በተጨማሪ ወጪ ሆኖ በፌዴራሉ መንግሥት እንዲከፈል በዚህ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

**አንቀፅ ፫** ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት ከፌዴራል መንግሥት ገቢ በዚህ አዋጅ ለተጨማሪ ሥራዎች የተፈቀደላቸውን ተጨማሪ በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትሩ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል፡፡

**አንቀጽ ፬** በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የተጨማሪ በጀት በ፪ሺ፲፫ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፩/፪ሺ፲፪ በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም.**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Article 2** There is hereby appropriated a Supplementary budget on the 2013 approved budget to the Federal Government, for the Fiscal Year commencing on Hamle 1, 2012 E.C and ending on sene 30,2013 E.C., from Federal Government Domestic Revenue ፦

| | | |
|---|---|---|
| (A)For Recurrent Expenditures | Birr | 25,833,000,000 |
| (B) For capital Expenditures | Birr | 602,375,000 |
| (C) Financing Restructuring | Birr | 12,044,900,000 |
| Total | Birr | 38, 480,275,000 |

Thirty Eight Billion Four Hundred Eighty Million Two Hundred Seventy Five Thousand Birr/ as set forth a schedule attached hereto.

**Article 3** The Minister of Finance is hereby authorized and directed upon the request of the heads of the concerned government organs, to disburse out of the Federal Government revenues the additional amount appropriated herein for the undertakings of their respective organs.

**Article 4** Utilization of the Supplementary Budget shall be made in accordance with the Budget Proclamation No 1221/2020.

**Done at Addis Ababa this 29th day of June 2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENTOF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**